# ማኅበራዊ ሚዲያ እና ማጋራት

ተሳታፊዎች በተለይም የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃ እንዴት እንደሚያጋሩ እና ከሌሎች ጋር እንዴት መረጃ እንደሚለዋወጡ ያስባሉ። በማኅበራዊ ሚዲያ ዐውድ ውስጥ በግላዊነት ውስጥ ስላለ ማቻቻል ማብራራት እና የመስመር ላይ የግላዊነት ቅንብሮችን እንዴት በውጤታማነት መጠቀም እንደሚችሉ ይማራሉ።

# የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

## ክፍል አንድ

### የክላስ መስተጋብር

ከሚቀጥለው መልመጃ በፊት፣ በክፍሉ ተቃራኒ ጥጎች "እስማማለሁ" እና "አልስማማም" የሚሉ ጽሁፎች ይለጥፉ። እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ካነበቡ በኋላ ተሳታፊዎች ወደ አንዱ ጥግ ወይም ወደ ሌላኛው አጠገብ በስሜታቸው መጠን ልክ እንዲጠጉ ያሳውቋቸው፤ ተሳታፊዎች ካልወሰኑ ወይም እርግጠኛ ካልሆኑ በሁለቱ ምልክቶች መካከል ላይ መቆም ይችላሉ።

በዓረፍተ ነገሮቹ መካከል፣ አቋማቸውን እንዲያብራሩና ስለ እያንዳንዱ ርዕስ ቡድኑን እንዲያሳትፉ ይጠይቋቸው።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

አንድ አረፍተ ነገር ላነብብ ነው። መቶ በመቶ የሚስማሙ ከሆነ ፣ ወደ "እስማማለሁ" ምልክት ይሂዱ። ሙሉ ለሙሉ የማይስማሙ ከሆነ፣ ወደ "አልስማማም" ምልክት ይሂዱ። እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁ / አልስማማም የማይሉ ከሆነ፣ የእርስዎን ሃሳብ በሚወክል መጠን ወደ መካከል ይጠጉ።

እንደ Facebook፣ Twitter, Snapchat, ወይም Instagram ያሉ ማኅበራዊ ሚድያዎች ላይ መለያ አለኝ።

ማኅበራዊ ሚዲያ በየቀኑ እጠቀማለሁ።

በብዛት በምጠቀምበት ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የማኅበራዊ ሚዲያ መገለጫዬ ይፋዊ ነው።

በምጠቀምባቸው የተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ የተለያዩ ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች (በሌላ አነጋገር የተለያዩ እድምተኞች) አሉኝ።

ከአዋቂዎች ጋር ሲነጻጸር በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ስለሚጋራ መረጃ የእኔ ትውልድ የተለየ መገድ አለው።

የተለዩ አይነት ይዘቶችን ለማጋራት የተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን እጠቀማለሁ።

# የጓደኝነት ጥያቄ ኀብረቀለም

## ክፍል አንድ

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

*የማኅበራዊ ሚድያ መድረክ ከሰዎች ጋር የሚገናኙበት እና ምልልሶችን የሚያደርጉበት የመስመር ላይ መድረክ ነው።*

### *ተማሪዎችዎን ይጠይቁ*

እርስዎ የሰሚቸው አንዳንድ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች እንደማን ናቸው?

## ክፍል ሁለት

### የክላስ መስተጋብር

ከሚቀጥለው መልመጃ በፊት፣ በክፍሉ ተቃራኒ ጥጎች "እስማማለሁ" እና "አልስማማም" የሚሉ ጽሁፎች ይለጥፉ። እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ካነበቡ በኋላ ተሳታፊዎች ወደ አንዱ ጥግ ወይም ወደ ሌላኛው አጠገብ በስሜታቸው መጠን ልክ እንዲጠጉ ያሳውቋቸው፤ ተሳታፊዎች ካልወሰኑ ወይም እርግጠኛ ካልሆኑ በሁለቱ ምልክቶች መካከል ላይ መቆም ይችላሉ።

በዓረፍተ ነገሮቹ መካከል፣ ከእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ከቡድኑ ጋር አጭር ውይይት ያድርጉ።

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

*አንድ አረፍተ ነገር ላነብብ ነው። መቶ በመቶ የሚስማሙ ከሆነ ፣ ወደ "እስማማለሁ" ምልክት ይሂዱ። ሙሉ ለሙሉ የማይስማሙ ከሆነ፣ ወደ "አልስማማም" ምልክት ይሂዱ። እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁ / አልስማማም የማይሉ ከሆነ፣ የእርስዎን ሃሳብ በሚወክል መጠን ወደ መካከል ይጠጉ።*

*ለዚህ መልመጃ፣ በአብዛኛው ስለሚጠቀሙበት የማኅበራዊ ሚዲያ መለያዎ ያስቡ።*

### *ተማሪዎችዎን ይጠይቁ*

የእኔ ማኅበራዊ ሚድያ መገለጫ ይፋዊ ነው።

1. ይህ በመስመር ላይ የሚለውጧቸውን ነገሮች ይለውጣል? ያ እንዴት ይሆናል? ወይም ካልሆነ ደግሞ፣ ለምን አልሆነም?

የእኔ የማኅበራዊ ሚዲያ መገለጫ ለጓደኞች / በደንብ ለማውቃቸው ሰዎች ብቻ ነው።

1. ይህን ውሳኔ ለምን ወሰዱ?
2. ሁሉም ሰው የሚያየው ቢሆን ኖሮ የተለያዩ ነገሮችን ይለጥፉ ነበር? ምን አይነት ነገሮች?

በገሃዱ ዓለም አግኝቸው የማላውቀው ጓደኛ / ተከታይ / ግንኙነት በማኅበራዊ ሚድያ ላይ አለኝ።

1. ከዚህ ሰው ጋር ለምን ጓደኛ ሆኑ / ተከተሉ / ተገናኙ? በመስመር ላይ ያገኙት እና ከዚያ በፊት አግኝተውት የማያውቁት ሰው ነው?
2. ግንኙነቱን እንዴት ይገልጹታል?
3. በመስመር ላይ ብቻ የሚገናኙ በመሆኑ፣ እንዴት እንደሚነጋገሩ ተጽዕኖ ያሳድርብዎታል? እንዲህ ያለ ንግግር ጥቅሞቹ ምንድናቸው? ሊሆኑ የሚችሉ ፈተናዎቹስ?

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

የሚደርሰኝን ሁሉንም የጓደኝነት / የመከተል / የመገናኘት ጥያቄ እቀበላለሁ።

1. የዚህ አቀራረብ ጥቅም ምንድነው? ሊሆኑ የሚችሉ ፈተናዎቹስ?
2. በግላዊነት ጉዳይ ላይ የጓደኛ / ተከታይ / ግንኙነት ጥያቄዎች ተጽዕኖ ይኖራቸዋል? ከሆነ፣ እንዴት? ካልሆነ ደግሞ፣ ለምን አልሆነም?

አዲስ ጓደኞች በማገኝ ጊዜ ሁሉ የጓደኝነት/ የመከተል / የግንኙነት ጥያቄ እልክላቸዋለሁ።

1. ይህ ለምን ጥሩ / መጥፎ ሃሳብ ሆነ?

ጓደኞችን / ተከታዮችን / ግንኙነቶችን ሰርዣለሁ። 1. ይህን ውሳኔ ለምን ወሰዱ?

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

እኔ በመስመር ላይ ከወላጆቼ / አሳዳጊዎቼ ጋር ጓደኞች ነኝ?

1. ይህ የሚለጥፉበትን መንገድ ይለውጥቦታል?
2. በሕይወትዎ ውስጥ ያሉ አዋቂ ሰዎች በመስመር ላይ በሚለጥፏቸው ነገሮች ላይ አስተያየቶችን ይሰጣሉ?
3. ከወላጆች /አሳዳጊዎች ጋር ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነት ያለዎት መሆኑ ጥቅሞቹ እና / ወይም ፈተናዎቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

በመገለጫዬ ላይ ያሉ የተወሰኑ ነገሮች በጓደኞች ጓደኞች / በቀጥታ ባልተገናኘኋቸው ሰዎች ሊታዩ ይችላሉ።

1. የትኞቹ ነገሮች?

የግላዊነት ቅንብሮቼን ተመልክቼ ቀይሬያቸዋለሁ።

1. ለምን አደረጉ፣ ወይም ለምን አላደረጉም?
2. እነዚህ የግላዊነት ቅንብሮች ቀላል ነበሩ ወይስ ግራ አጋቢ? እነዚህን ቅንብሮች ለመመልከት / ለመለወጥ ምን ቀላል ሊያደርጋቸው ይችላል?

# አውታረ-መረብዎ ምን ያህል ትልቅ ነው?

## ክፍል አንድ

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

*አሁን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ስላለዎት ታዳሚ አድማስ እናውራ።*

ይዘት(ለምሳሌ፣ ምስል፣ ቪድዮ፣ ጽሑፍ ላይ የተመሰረቱ ልጥፎች) ለታዳሚ የሚጋራባቸው መንገዶች በተመለከተ ሁለት አበይት መንገዶች አሉ። አንድ ይዘት ለነባር ታዳሚ ማለትም ጓደኞች / ተከታዮች / ሊጋራ ወይንም የጓደኞች ጓደኞችን ሊያጠቃልል ይችላል። ሁለት፣ የመጀመሪያዎቹ ታዳሚዎች ይዘቱን ለጓደኞቻቸው / ተከታዮቻቸው ሊያጋሩ ይችላሉ።

የቀጥታ ታዳሚዎ ሊመርጡ ይችላሉ ነገር ግን ታዳሚዎ ይዘትዎን ምንያህል እንደገና እንደሚያጋራው / መልሶ እንደሚለጥፈው / መልሶ ትዊት እንደሚያደርገው መቆጣጠር አይችሉም።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

እርስዎ አንድን ይዘት ከተገናኙዋቸው ጓደኞች / ተከታዮች / ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ጓደኞች / ተከታዮች / ጋርም ቢያጋሩት፣ ከስንት ሰዎች ጋር ያጋሩት ይመስሎታል?

## ክፍል ሁለት

**የክላስ መስተጋብር**

የሚከተሉትን ቀመሮች / ውጤቶች በሰሌዳው ላይ ይጽጻፉ። ***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

ትንሽ ሂሳብ እንስራ ለምሳሌ፣ እርስዎ በማህበራዊ ሚድያ ሁለት ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች አሎዎት፣ እነዚህ እያንዳንዳቸው ደግሞ ሶስት ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ካሉዋቸው፣ በዛ ቢባል ስንት ሰዎች (የተወሰኑ ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ምናልባት ሊደራቡ ይችላሉ) ፕላትፎርሙ ላይ የእርስዎን ይዘት ሊያዩ ይችላሉ?

1. መልስ፦ 2 + 2 x 3 = 8

ለምሳሌ፣ እርስዎ በማህበራዊ ሚድያ አስር ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች አሎዎት፣ እነዚህ እያንዳንዳቸው ደግሞ ሶስት ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ካሉዋቸው፣ በዛ ቢባል ስንት ሰዎች (የተወሰኑ ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ምናልባት ሊደራቡ ይችላሉ) ፕላትፎርሙ

ላይ የእርስዎን ይዘት ሊያዩ ይችላሉ? 1. መልስ፦ 10 + 10 x 10 = 110

ለምሳሌ፣ እርስዎ በማህበራዊ ሚድያ መቶ ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች አሎዎት፣ እነዚህ እያንዳንዳቸው ደግሞ ሶስት ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ካሉዋቸው፣ በዛ ቢባል ስንት ሰዎች (የተወሰኑ ጓደኞች / ተከታዮች / ግንኙነቶች ምናልባት ሊደራቡ ይችላሉ) ፕላትፎርሙ ላይ የእርስዎን ይዘት ሊያዩ ይችላሉ?

1. መልስ፡- 300 + 300 x 300 = 90,300

**ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው**

እነዚህ ስሌቶች የእርስዎ ቀጥተኛ ታዳሚዎች በበኩላቸው የእርስዎን ይዘት ለቀጥታ ታዳሚዎቻቸው ያጋራሉ፣ ከዛ በኋላ ግን ማጋራቱ ይቆማል በሚል ታሳቢ ነው የተሰሉት። ይሁን እንጂ፣ በብዙ አጋጣሚዎች፣ ይዘቱ ከሁለቱም ቀጥተኛ ታዳሚዎች ባሻገር ጭምር ሊጋራ ይችላል።

# ክፍል 3

**ተማሪዎችዎን ይጠይቁ**

በመስመር ላይ የሚሰሩትን ሥራ ይህን ያህል የማያውቋቸው (የተወሰኑትን የጓደኞችዎን ጓደኞች ሊያውቋቸው ይችላሉ) ማወቃቸው ምን ስሜት ይፈጥርብዎታል? የዚህ አንዳንድ አወንታዊ እና/ወይም አሉታዊ ገጽታዎች የትኞቹ ሊሆኑ ይችላሉ?

ይህ ለምን ይጠቅማል?

ይህ በመስመር ላይ የሚያጋሯቸውን ነገሮች ይለውጣል? ለምን፣ ወይም ለምን አይሆንም?

# በመስመር ላይ ማጋራት

## ውይይት አንድ

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

ለታሰቡ አድምተኞች በመስመር ላይ ነገሮችን ሊያጋሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን፣ አንድን ይዘት ይፋዊ ሲያደርጉ፣ ያልተጠበቀ ትኩረት ሊያገኝ ይችላል።

በመስመር ላይ የተጋራ ይዘት በማኀበራዊ ሚድያ ላይ እየተባዛ እና ምናልባትም እየተቀናበረ በፍጥነት እንደ ቫይረስ ሊዛመት ይችላል።

### ተማሪዎችዎን ይጠይቁ

የተዛማች ሚዲያ ምሳሌ ማሰብ የሚችል ሰው አለ?

1. ከሌለ፣ ስለ ሚሞች፣ ቅንብሮች፣ ወይም ስላዩአቸው እና ለጓደኞቻቸው ስላጋሯቸው በጣም ተወዳጅ የሆኑ ቪዲዮዎች ይጠይቋቸው።

## መስተጋብር

### የክላስ መስተጋብር

ንድፈ-ሀሳቡን የበለጠ ለማጠናከር ከእርስዎ / ተሳታፊዎች አካባቢያዊ / ዞናዊ አውድ ጋር የተቆራኘ የቅርብ ጊዜ ምሳሌ ያሳዩ።

## ውይይት ሁለት

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

*ተዛማች ሚዲያ ወደ ሥራዎ ትኩረት ለመሳብ ከፈለጉ ጥሩ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ያልተፈለገ ትኩረት፣ ምናልባት ወከባ እና የመስመር ላይ ማስፈራራት ሊያስከትል ይችላል። ያለፈቃድዎ ከእርስዎ ተሰርቆ የተጋራ የግል ቪዲዮዎ መልካም ዝናዎን የሚያበላሽ ሊሆን ይችላል።*

### *ተማሪዎችዎን ይጠይቁ*

ስለ እርስዎ የሚናገር ይዘት እርስዎ ካሰቡት ታዳሚ ባሻገር እንዲዳረስ ማድረጊያ አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?፣

ይህ እንዴት እርስዎና መልካም ስምዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል?

# የግላዊነት አማራጮች ለማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች

## ክፍል አንድ

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

አሁን በመስመር ላይ የሚሰሯቸው ሥራዎች በሙሉ ለምን ይፋዊ እንዲሆን እንደማይፈልጉ ተነጋግረናል፣ አሁን እንዴት በመስመር ላይ ግላዊነታችንን ማስተዳደር እንደምንችል እንነጋገር።

## ክፍል ሁለት

**የክላስ መስተጋብር**

በጥያቄዎች መካከል፣ ከእያንዳንዱ ጥያቄ በታች ያሉ ዓረፍተ ነገሮች ላይ በመመስረት በውይይቱ ላይ ያብራሩ።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

ለተለያየ የመረጃ አይነት የተለያዩ የግላዊነት ቅንብሮችን ማዋቀር ስምሜት ይሰጣል?

1. የተለያዩ መረጃዎች የተለያዩ የግላዊነት ደረጃዎች እንዲኗቸው ሊገምቱ ይችላሉ። የፊትዎን ፎቶ፣ አንድ ትዊት ስለ ፖለቲካዊ ወይም ኃይማኖታዊ ዕምነት፣ ወይም አንድ ታሪክ ወይም አስቂኝ ቪዲዮ ለተለያዩ ታዳሚዎች ማጋራት ይፈልጉ ይሆናል፣

ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ የግላዊነት ቅንብሮች የሚለውስ? ለምሳሌ፣ ወላጆችዎ / አሳዳጊዎችዎ እና ጓደኞችዎ በማኅበራዊ ሚዲያ መለያዎችዎ ላይ ተመሳሳይ ነገር ያያሉ?

1. ተሳታፊዎች ቤተሰቦቻቸው በልጥፎቻቸው ላይ አስተያየት መስጠት እንዳይችሉ ጓደኞቻቸው ግን ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ሊፈልጉ ይችላሉ።

እርስዎ የተጠቆሙባቸውን ነገሮች ሁሉ ወደኋላ ተመልሰው ገምገመው ያውቃሉ? ለምን አደረጉ፣ ወይም ለምን አላደረጉም?

1. ማንኛውንም የሚያሳፍር ይዘት (ለምሳሌ፣ ተንጨባረው የተነሱት ፎቶ፣ ወይም እርስዎ እንዲጋራ የማይፈልጉት ልጥፍ)። ማስወገድ ይፈልጉ ይሆናል።

በአንዳንድ የማኅበራዊ መረብ ሚዲያ መድረኮች፣ ለምሳሌ Facebook፣ በመገለጫዎ ላይ ከመታየቱ በፊት የእርስዎ ፈቃድ እንዲጠየቅ አድርገው ማዋቀር ይችላሉ። ያ ጥሩ ሃሳብ ይመስልዎታል? ለምን ሆነ፣ ወይም ለምን አልሆነም?

1. አሳፋሪ ይዘት ከእርስዎ የማኅበራዊ ሚዲያ መለያ ጋር እንዳይያያዝ ለመከልከል ያግዝዎታል። ነገር ግን፣ ለጣፊው ሰው በራሱ መለያ ላይ ለጓደኞቹ / ለተከታዮቹ / ለተገናኛቸው ሰዎች ከማጋራት አይከለክልም።

አንድ ሰው ማን ፈልጎ ሊያገኘው እንደሚችል ለምን መገደብ ይፈልጋል? ምሳሌ መስጠት ይችላሉ?

1. የማያውቋቸው ሰዎች / ጓደኛ ለማድረግ / ለመከተል / በደንብ የማያውቋቸው ሰዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ከእርስዎ ጋር እንዲገናኙ ወይም የማይፈልጓቸውን መልዕክቶች እንዲልኩልዎ ላይፈልጉ ይችላሉ።

እርስዎ በመስመር ላይ ከወላጆችዎ / አሳዳጊዎችዎ ጋር ጓደኞች ናችሁ? መምህራን? ሌሎች አዋቂ ሰዎች?

1. ይህ የሚያጋሩትን ይዘት ወይም ይዘቱን ለማን እንደሚያጋሩ ይቀይረዋል?

ወላጆች / አሳዳጊዎች ወይም መምህራን መገለጫዎን ለማግኘት ከእርስዎ ጋር ጓደኛ መሆን / መከተል / መገናኘት ይፈልጋሉ?

1. ተሳታፊዎች የራሳቸው የግላዊነት ቅንብሮች የማኅበራዊ ሚዲያ መገለጫዎቻቸው ሕዝብ እንዲያየው የሚፈቅዱ እንደሆነ ማየት አለባቸው። ወላጆች / አሳዳጊዎች ወይም መምህራን የእነርሱን መገለጫዎች ማየት ስለሚችሉባቸው መንገዶች እንዲያስቡ ይርዷቸው።

ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች የሚለውስ? በTwitter ላይ፣ የእርስዎ ትዊቶች የግል ናቸው ወይስ ይፋዊ? የእርስዎን ቅጽበታዊ ታሪኮች ስንት ሰዎች ይመለከቱታል? ምን ያህል ሰዎች የእርስዎን የInstagram ምግብ የመለከታሉ? ሌሎች ሰዎች የእርስዎን ቪዲዮ በYouTube ላይ መመልከት ይችላሉ? ሰዎች በFacebook ላይ፣ ከመገለጫ ፎቶዎችዎ ባሻገር ያሉ ፎቶዎችዎን መመልከት ይችላሉ?

1. ተሳታፊዎች የማያውቁ ከሆነ፣ ለዚህ የግላዊነት አንብሮች እንዳሉ ይንገሯቸው።

ትዊት የሚያደርጉት በእራስዎ ስም ነው ወይስ በብዕር ስም? ለምን?

1. ተሳታፊዎች ሕዝቡ እውነተኛውን ስማቸውን እንዲያውቅ አይፈልጉም ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የብዕር ስም ይጠቀማሉ።

## ክፍል ሶስት

**የክላስ መስተጋብር**

*ተሳታፊዎችን በጥንድ እያደረጉ ያደራጁ*

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

የግላዊነት ቅንብሮች ግራ አጋቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ እናውቃለን።

በእርስዎ ጥንድ ውስጥ፣ ስለ የግላዊነት ቅንብሮች አንድ ጥያቄ ለማምጣት የተወሰኑ ደቂቃዎች ይውሰዱ።

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎች ስለ የግላዊነት ቅንብሮች አንድ ጥያቄ እንዲያመጡ ወይም በግላዊነት ቅንብሮች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ 5 ደቂቃዎች ይስጧቸው። ለሁሉም ቡድን እንዲያጋሩ እና እያንዳንዱን የተጠቀመ ጥያቄ እንዲመልሱ ያድርጓቸው። የእርስዎን መልስ ከመስጠትዎ በፊት ሌሎች ተሳታፊዎች መልስ እንዲሰጡ ዕድል ይስጡ።

ኮምፒውተሮች ወይም የበይነመረብ መዳረሻ ያላቸው ሞባይል መሳሪያዎች ካሉ፣ በመስመር ላይ የግላዊነት ቅንብሮችን እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል ያሳዩ።

# ምድብ ሥራ

## መምሪያ

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

አሁን ስለ ማኅበራዊ ሚዲያ ግላዊነት ተነጋግረናል፣ እና እርስዎ አሁን የተማሩትን ሌሎች እንዲማሩት የሚረዳ መምሪያ በማዘጋጀት እናስፋው።

በሚቀጥሉት 30 ደቂቃዎች ውስጥ፣ ሌሎችን ለመርዳት አጭር መምሪያ ይፍጠሩ፦

1. ስለ የማኅበራዊ ሚዲያ ልጥፎቻቸው ታዳሚዎች ያስቡ።
2. በይፋ ማጋራት የሚፈልጉት ምን እንደሆነ እና ለግላቸው መያዝ የሚፈልጉት የቱ እንደሆነ ያሰላስሉ።
3. የማኅበራዊ ሚዲያ የግላዊነት ቅንብሮቻቸውን ለምን መገምገም እና አርትዕ ማድረግ ሊፈልጉ እንደሚችሉ ያስቡ።
4. የተለያዩ የግላዊነት ቅንብሮችን ለተለያየ ይዘት እንዴት ማዋቀር እንደሚችሉ እና ለምን ያንን ማድረግ ሊፈልጉ እንደሚችሉ ይመርምሩ።

ይህ መምሪያ እርስዎን በፈለጉት ቅርጸት ሊዘጋጅ ይችላል። የደረጃ በደረጃ የጽሁፍ መምሪያ መጻፍ፣ እንደ "የተጠቃሚ መመሪያ" ማዘጋጀት፣ ምስሎችን እና የፍሰት ገበታዎችን ማካተት፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሌሎች ይህን ለመማር ይረዳቸዋል ብለው የሚያስቡትን አይነት መንገድ መጠቀም ይችላሉ፤ ፈጠራዎን ለመጠቀም ነጻነት ይሰማዎት! በመምሪያው ውስጥ፣ የሚከተሉት መደረጋቸውን ያረጋግጡ፦

1. አንባቢዎች በማኅበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ እንዴት የግላዊነት ቅንብሮችን መገምገም እና መለወጥ እንደሚችሉ ማሳየት።

2. ቀደም ብሎ በነበረ የቡድን ውይይት መሰረት ስለ የግላዊነት ቅንብሮች አስፈላጊ ነው ብለው ለሚያምኑት ጥያቄ ምላሽ ማቅረብ።

### ምድብ ስራ

በአጠቃላይ የተለያዩ መድረኮች እንዲሸፈኑ ተሳታፊዎች የተለያዩ መድረኮችን እንዲመርጡ ማበረታታት። ተሳታፊዎች ሥራውን እንዲጨርሱ 30 ደቂቃ መስጠት።

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።